# የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትርና የኃይለማርያምና ሮማን ፋዉንዴሽን የቦርድ ሊቀመንበር

# አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ በደ/ብ/ብ/ክልል በደቡብና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች

# ከየካቲት 29/2012 ዓ.ም እስከ መጋቢት 6/2012 ዓ.ም ድረስ ያደረጉት የመስክ ጉብኝት

# አጭር ሪፖርት

መጋቢት 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

## ማዉጫ

**1.መግቢያ** **1**

2. የጉብኝቱ ዓላማዎች **1**

3. የአካባቢዎቹ አጭር መግለጫ **2**

4. የቡድኑ ምልከታዎች፤ የተነሱ ችግሮችና የመፍትሔ ጥቆማዎች **3**

4.1 በደቡብ ኦሞ ዞን በሀመርና ዳሰነች አካባቢዎች በተደረገ ጉብኝት የታዩ እዉነታዎች፥ ችግሮች፤ የተቀመጡ መፍትሄዎችና ምክረሃሳቦች 3

4.2 በኦሞ ብሔራዊ ፓርክ በተደረገ ጉብኝት የታዩ እዉነታዎች፤ ችግሮች፤ የተቀመጡ መፍትሄዎችና ምክረሃሳቦች 7

4.3 በማጎ ብሄራዊ ፓርክ በተደረገ ጉብኝት የታዩ እዉነታዎች፤ ችግሮች፤ የተቀመጡ መፍትሄዎችና ምክረሃሳቦች 13

5.ማጠቃለያ **16**

# 1.መግቢያ

በቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ እና በባለቤታቸው የቀድሞ ቀዳማዊት እመቤት ወ/ሮ ሮማን ተስፋዬ የተቋቋመው የኃይለማርያም እና ሮማን ፋውንዴሽን በእናቶች፥ ህጻናት ጤና እና ስርዓተ ምግብ፤ ብዝሃ ህይወት ጥበቃን መሰረት ያደረገ ኢኮቱሪዝም እና የሴቶችና ወጣቶች ስራ ፈጠራ ላይ ትኩረት አድርጎ በኢትዮጵያ በተለይ ልዩ ድጋፍ በሚሹት አፋር፥ ጋምቤላ፥ ቤንሻንጉል ጉምዝ እና ከደቡብ ክልል በደቡብ ኦሞ ዞን፥ በምዕራብ ኦሞ ዞን እና በኮንታ ልዩ ወረዳ ውስጥ፤ እንዲሁም በአጠቃላይ በአፍሪካ ቀንድ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል።

ፋውንዴሽኑ በሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ፓርኮችን መሰረት አድርጎ የሚሰራቸውን አሳታፊ የብዝሃ ህይወት ጥበቃና ኢኮቱሪዝም ስራዎች ለመጀመር እንዲረዳ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ራሳቸው የመሩት አንድ ሳምንት የፈጀ የመስክ ጉብኝት በጨበራ ጩርጩራ እና ማዜ ብሄራዊ ፓርኮች ከጥቂት ሳምንታት በፊት ተደርጎ የነበረ ሲሆን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አህመድ ከቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ጋር በመሆን ከደቡብ ኦሞ ዞን ነዋሪዎች ጋር በጂንካ ከተማ ያደረጉትን ህዝባዊ ዉይይት ተከትሎ የቀድሞዉ ጠቅላይ ሚኒስትር ለተከታታይ ስምንት ቀናት በመላው ደቡብ ኦሞ ዞን እና ምዕራብ ኦሞ ዞን እንዲሁም በኦሞ ብሔራዊ ፓርክ እና ማጎ ብሄራዊ ፓርክ ጥልቅ የመስክ ጉብኝት አድርገው ነበር። በቀድሞ ጠቅላይ ሚንስትር በተመራዉ በዚሁ ጉብኝት ከፋዉንዴሽኑ በኩል ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ የየዘርፍ ሃላፊዎች የተሳተፉ ሲሆን ከመንግስት በኩል የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን (ኢዱልጥባ) ዋና ዳይሬክተር በአቶ ኩመራ ዋቅጅራ የተመራዉ የዘርፍ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ቡድን እንዲሁም የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የኦሞ ኩራዝ ፕሮጀክቶች ሃላፊዎች ተሳትፈዉበታል።

## 2. የጉብኝቱ ዓላማዎች

የግብኝቱ ዋነኛ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ፤

- በአካባቢው የሚገኙ ብሄራዊ ፓርኮች እና በፓርኮቹ ዙሪያ ያሉ ማህበረሰቦች እንዲሁም መንግስታዊ ሜጋ ፕሮጀክቶችን በአካል ተገኝቶ በመጎብኘትና ነባራዊ ሁኔታዉን በጥልቀት በመረዳት በቀጣይ መንግስትና ፋዉንዴሽኑ በጋራ በአካባቢዉ ሊሰሯቸዉ ላሰባቸዉ ስራዎች ግብዓት ማግኘት፤

- ብሄራዊ ፓርኮቹ ያሉባቸውን ችግሮች በመለየት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የመፍትሔ አቅጣጫ ለማስቀመጥና ለመተግበር እንዲሁም ለአካባቢዉ ማህበረሰብ ዘላቂ ብልጽግና የተለያዩ ድጋፎችን ለማስተባበር፤

## 3. የአካባቢዎቹ አጭር መግለጫ

በቀድሞ አከላለል የደቡብ ኦሞ ዞንና ቤንች ማጂ በሚል ተዋቅረው ይገኙ የነበሩት አካባቢዎች አሁን ደቡብ ኦሞ እና ከቤንች ማጂ የተከፈለዉ የምዕራብ ኦሞ ዞን ተከፋፍለው የተደራጁ ይሁኑ እንጂ በመልክዓ ምድር እና ማህበራዊ አሰፋፈር እንዲሁም የአኗኗር ሁኔታ ተቀራራቢ ናቸው።

የደቡብ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች የድንበር አካባቢ ዞኖች እንደመሆናቸዉ መጠን ደቡብ ሱዳን እና ኬንያ ያዋስኗቸዋል። ዞኖቹ በብዛት በደን የተሸፈኑ እና በተራራቀ ሁኔታ የሚኖሩ አርብቶ አደር ማህበረሰቦች የሚኖሩባቸው ሲሆኑ ተራሮችን፥ ወንዞችን እና ሜዳዎችን በስፋት የያዙ ናቸው።

በዞኖቹ ሐመር፥ አሪ፥ ማሌ፤ ካሮ፥ ሙርሌ፤ ብራይሌ፤ ኛንጋቶም፥ መኢኒት፥ ሙርሲ፥ ሱርማ፥ ዲሜ፤ ዲዚ፥ ባጫ፥ ቦዲ፥ ኤርቦሬ፥ ኮይጉ፥ በና፥ ጸማይ እና ዳሰነች የተባሉ ብሔረሰቦች ይኖሩባቸዋል። እነዚህ በሁለቱ ዞኖች የሚገኙ 19 የሚደርሱ ብሔረሰቦች ባብዛኛዉ የኦሞቲክ እንዲሁም የተወሰኑት የኒሎ ሰሃራዊና ኩሽቲክ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሲሆኑ የአንድ ቤተሰብ ያህል ተቀራራቢነት ያላቸው ናቸው። ከነዚህ ዉስጥ የኒሎሳሃራዊ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑት ሙርሲ፤ ሱርማ፤ ኛንጋቶም፤ ኪዮጉ፤ ቦዲ፤ ሙርሌና ባጫ ሲሆኑ አሪ፤ በና፤ ካሮ፤ ሀመር፤ ማሌ፤ ዲሜ፤ ዲዚ፤ እና መኢኒት የኦሞቲክ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸዉ፤፤ ቀሪዎቹ ዳሰነች፤ጸማይ፤ ኤርቦሬና ብራይሌ ደግሞ የኩሽቲክ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸዉ።

የአካባቢው ነዋሪዎች በአካባቢው የሚገኘውን ሰፊ የቀንድ እና የዳልጋ ከብት ሃብት መሰረት ያደረገ በብዛት የአርብቶ አደርነት ስራ ላይ የተሰማሩ ሲሆን በተለይ የአሪና ማሌ ማህበረሰቦች ጥምር ግብርና ስራን ያከናውናሉ። እንደየአየር ጠባዩ እና የመሬት አቀማመጥ አመቺነቱ የእህል ሰብሎች በተለይም ማሽላ፥ በቆሎ፥ ጤፍ እና የተለያዩ ፍራፍሬዎች እንዲሁም ጥጥ፤ሰሊጥ ጥራጥሬዎችና ሸንኮራአገዳ ቡናና እንሰት የመሳሰሉ ሰብሎች ይመረታሉ።

## 4. የቡድኑ ምልከታዎች፤ የተነሱ ችግሮችና የመፍትሔ ጥቆማዎች

### 4.1 በደቡብ ኦሞ ዞን በሀመርና ዳሰነች አካባቢዎች በተደረገ ጉብኝት የታዩ እዉነታዎች፥ ችግሮች፤ የተቀመጡ መፍትሄዎችና ምክረሃሳቦች

በዞኖቹ የሚገኙት የኦሞና የማጎ ብሄራዊ ፓርኮች እንዲሁም የታማ ጥብቅ ደንን ጨምሮ የ19ኙ ብሔረሰቦች የአኗኗር ዘይቤ እና በታችኛው ኦሞ የሚገኘው የፓሊዮንቶሎጂ ሳይት ለቱሪስቶች እጅግ በጣም ሳቢ እና በስብጥር አስደሳች ቆይታን የሚሰጡ መስህቦች ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ መስህቦች በአንድ በኩል ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ በእጅጉ የሚጎላቸው ሲሆን በሌላ በኩል ቱሪስቶችን በምቾት ሊያስተናግዱ የሚችሉ ሎጆች፥ ማረፊያዎች እና መሰረተልማቶች አልተሟሉላቸዉም። በተጨማሪም የቱሪስት መስህቦቹን የማስተዋወቅ ስራም ገና አልተሰራም። በተለይ በአሁኑ ጊዜ በይበልጥ በቱሪስቶች እየተጎበኙ የሚገኙ እንደ ሐመር እና ካሮ የመሳሰሉ ማህበረሰቦች ከሚገኘው የቱሪስት ገቢ ተገቢዉን ጥቅም እያገኙ አለመሆኑን በጉብኝታችን ወቅት ታዝበናል።

በሐመር እና በካሮ ማህበረሰብ አካባቢ ያሉትን ችግሮች ተቋቁሞም ቢሆን ጥሩ የቱሪስት ፍሰት ያለ ቢሆንም የማህበረሰቦቹ ተጠቃሚነት ግን ገና ብዙ መስራት የሚጠይቅ እንደሆነ ታዝበናል። ከመንገድ የመሰረተ ልማት ችግር በተጨማሪ እነዚህ አካባቢዎች የዞኑ ዝቅተኛና ዉሃ አጠር አካባቢዎች በመሆናቸው ሰፊ የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት ችግር ገጥሟቸው ይታያል። በዚህም ሳቢያ ለቤት እንስሳቱም ሆነ ለሰው የሚሆን ዉሃ በቅርብ ስለማያገኙ ከስፍራ ስፍራ ሲንከራተቱ ይኖራሉ።

በሌላ በኩል አካባቢው ከፍተኛ የሆነ ዝናብ የሚዘንብበትና እሱን ተከትሎ ለሚመጣ ጎርፍ የተጋለጠ በመሆኑ በስነ ምህዳሩ ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት አፋጣኝ መፍትሔ ካልተበጀለት መጠነ ሰፊ ጉዳት ማስከተሉ ስለማይቀር በሌሎች የሃገራችን መሰል አካባቢዎች የተሰሩ ልምዶችን መነሻ በማድረግ የዝናብ ውሃን ሊያቅቡ የሚችሉ አነስተኛ ግድቦችና ዘመናዊ ኩሬዎችን የመሳሰሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ዓመቱን በሙሉ ዉሃ እንዲያገኙና አካባቢያቸውን እንዲጠብቁ ማድርግ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። ለዚሁም በቅርቡ የዉሃ ልማት ዲዛይን ኮርፖሬሽን የጥናት ሥራ እንደጀመረ የተነገረን በመሆኑ ይኸዉ ተፋጥኖ ወደተግባር እንዲቀየር ምክረሃሳብ እናቀርባለን። ዉኃን ማዕከል ካደረገ ልማት ዉጭ የሚታሰብ ነገር በዚሁ አካባቢ ዘላቂ አይደለምና።

ይህ ዉሃን መሰረት ባደረገ መልኩ የሚሰራ ስራ አርብቶ አደሩን በአንድ አካባቢ በማሰባሰብ ከዳሰነች ማህበረሰብ በተገኘ ልምድ መሰረት በከፊል ግብርና ስራ እንዲሰማሩ እድል የሚፈጥር ከመሆኑም ባሻገር

በተደራጀ አኳኋን የቱሪስት ገቢን በማሳደግ ይህኑም ለላቀ ልማታዊ ጠቀሜታ የሚያውሉበት ኮምፕሪሄንሲቭ እቅድ ተዘጋጅቶ ሊተገበር እንደሚገባ ታዝበናል።

በነዚህ አካባቢዎች የህዝቡን ከቱሪዝም ልማት ተጠቃሚነት ለማሳደግ መነሻ የሚሆኑ ጥሩ ጅማሬዎች መኖራቸውንም ታዝበናል። ለአብነት ያህል በሐመር ቱርሚ ከተማ እና አካባቢው ላይ የሚንቀሳቀስ ኢቫንጋዲ ቱር ኦፕሬተርስ ማህበር በራሱ በአርብቶ አደሩ ልጆች የተቋቋመ ሲሆን ዋና አገልግሎቱ የቱር ጋይድ አገልግሎት መስጠትና እንደኢቫንጋዲ ያለውን ባህላዊ ጭፈራ ለቱሪስቶች በማቅረብ ላይ ያተኮረ ሆኖ አርዓያነት ያለውን ስራ እየሰራ ይገኛል። ማህበሩ ቱሪስቶችን መንደር ለመንደር አዟዙሮ ሲያስጎበኝ ከቱሪስቶች የሚሰበስበውን ገቢ በኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ የመቆጠብ ልምድም የጀመረ ሲሆን ይኸዉ ዳብሮ ከአካባቢ ልማት ጋር ቢያያዝ ህይወታቸውን በዘላቂነት ለመለወጥ እንደመልካም መነሻ ሊወሰድ ይችላል። በካሮ አካባቢም መሰል አደረጃጀቶች ያሉ ሲሆን በጥቅሉ ግን ሁለት መሰረታዊ ችግሮች ጎልተው ይታያሉ።

ከቱሪዝም የሚሰበሰበው ክፍያ ከሌሎች አገሮች አኳያ ሲታይ እጅግ አነስተኛ እና የማህበረሰቡን ህይወት የማይቀይር በመሆኑ በማህበረሰቡ ስነልቡና ላይ ስለቱሪዝም አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል። በሌላ በኩል የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ በተሻለ መልኩ ተደራጅቶ ፎቶ በመነሳት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ቱሪስቶች ሊገዟቸው የሚችሉ ቀላል ምርቶችን በማምረት ከቱሪስቱ ኪስ ተጨማሪ ገቢ የሚያገኝበት የክህሎት፥ የዕውቀትና የግብዓት ድጋፍ ስለማይሰጠዉ ከተለመደው ራቁትና በባህላዊ አርትና ጌጦች ያሸበረቀ ገላቸውን አሳይተው ከሚወረወርላቸው ዘመናዊ ባልሆነና የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን ባልተከተለ አኳኋን ከሚሰበሰብ ኢምንት ክፍያ የዘለለ ቱሪዝም የህይወት መቀየሪያ መንገድ እየሆነላቸው አለመሆኑን ታዝበናል።

በመሆኑም በአካባቢው የሚካሄደው ልማት ውሃን መሰረት ያደረገ የመንደር ማሰባሰብ ላይ ያተኮረ እንዲሆንና፤የቱሪስት ፓኬጅ ዝግጅቱም ተጨማሪ ገቢ በሚያስገኙ መንገዶች ፈርጀ ብዙ እንዲሆን ተገቢ ድጋፎች እንዲደረጉ፤ አሁን ያለው ክፍያ የሌሎች ሃገሮችን ልምድ በመውሰድ እንዲሻሻል የማህበረሰቡ አደረጃጀትም ተጨማሪ ክህሎትና ዝግጅት እንዲኖረው ቢደረግ ተገቢ መሆኑን ምልከታችንን እናስቀምጣለን።

በዳሰነች ማህበረሰብ በቱርካና ሃይቅ በኩል የኬንያ አጎራባች የሆነው ኦሞራቴ አካባቢ የሚገኙ አርብቶ አደሮች ወደከፊል ግብርና እንዲገቡ ተደርጎ በጣም ጠቃሚ ልምድ የተገኘ ሲሆን በተለይም በሙዝ ምርት ስራ ላይ በመሰማራት ሙዙ ለምርት ደርሶ አሁን ገበያ በማፈላለግ ላይ ይገኛሉ። ክቡር ጠ/ሚንስትር ዶ/ር አብይ ጂንካ

ከተማ ላይ ባደረጉት ዉይይትም ለሙዝ ምርታቸዉ ገበያ እንዲያፈላልጉላቸዉ በአጽንኦት ጠይቀዋል። ይሁን እንጂ ከሐመሯ የቱርሚ ከተማ እስከ ኦሞራቴ ድረስ ያለው መንገድ በጣም ጥሩ በሚባል ደረጃ ላይ የሚገኝ የአስፋልት መንገድ ሲሆን ከኦሞራቴ ከተማ አንስቶ በቅርብ ወደሚገኙት ሌሎች አጎራባች የኬንያ እና ከዚያም አልፎ እስከ ዩጋንዳ ድረስ የሚደርስ የመንገድ ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ ሙዛቸውን በውጪ ምንዛሪ መሸጥ አይችሉም። ይልቁንም ወደአዲስ አበባ ረጅም ርቀት አቋርጠው ቡብር ለመሸጥ እየተገደዱ ይገኛሉ። በአካባቢዉ ካሉ የግል ባለሀብቶች ጋር በአዉትግሮወር (outgrower) መልክ በመተሳሰር ምርቶቻቸዉን ለዉጭ ገበያ እንዲያቀርቡም ማመቻቸት አንዱ አማራጭ ሆኖ ይታያል። በቅርቡ ወደሙዝ ምርት እየገባ ያለ የዉጭ ኩባንያ እንዳለም በመስክ ጉብኝታችን የታዘብን ስለሆነ ይህኑ ማቀናጀት ጠቃሚ ይሆናል።

እንዲሁም በሌላ በኩል የዳሰነች ማህበረሰብ ከጥቂት ዓመታት በፊት ዓሣ የማይመገቡ የነበረ ቢሆንም ከሌላ አካባቢ በመጡ ሌሎች ማህበረሰቦች አማካይነት እንዲላመዱ ከተደረገ በኋላ በኢትዮጵያ በኩል ከሚገኘው በዓሣ ምርቱ ከሚታወቀው የሩዶልፍ (ቱርካና) ሐይቅ ዓሣ እያመረቱ መሸጥ ጀምረዋል። ይሁን እንጂ አሁንም ከኬንያ ጋር ያለው የመንገድ ግንኙነት ከባድ በመሆኑ በተሻለ ዋጋ እና በውጭ ምንዛሪ መሸጥ ሲችሉ እስካሁን ሳይሳካ ቀርቷል። ስለሆነም ከኬንያ እና ዩጋንዳ መንግስታት ጋር በመነጋገር ከኦሞራቴ እስከ ሎድዋር እና ሞሮቶ (እንደቅደም ተከተላቸው) የመንገድ ትይይዝ መፍጠር እነዚህን ሁለት ዋና ዋና ምርቶች ለመሸጥም ሆነ የረጅም ጊዜ የሃገር ለሃገር ትብብርን ከመፍጠር አኳያ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። ይህም በአፍሪካ ቀንድ የመሰረተ-ልማት ግንኙነት ማዕቀፍ ጋር ተያይዞ እንዲፈጥን ቢደረግ መልካም ነዉ እንላለን።

በተጨማሪም በአካባቢው አህዮች ለጭነት ግልጋሎት የማይውሉ ከመሆኑ የተነሳ ባለቤት እንኳን የሌላቸው እና በጣም በጥሩ አካላዊ ሁኔታና በመንጋ ደረጃ የሚገኙ ሲሆን ለዳሰነች ማህበረሰብ በአሁኑ ወቅት ምንም ገቢ እያስገኙ አይደለም። ይሁን እንጂ የዳሰነች ማህበረሰብ የአህያ ስጋ የሚመገብ በመሆኑ በዱከም አካባቢ ተቋቁሞ በአካባቢው ህዝብ ተቃውሞ ምክንያት የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት ሲችል ሳይሳካ የቀረው የአህያ ቄራ እዚህ አካባቢ ተዛዉሮ ቢቋቋም ወይም አዲስ ኢንቨስተር መሳብ ቢቻል ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል ታዝበናል።

ከዚህ ባሻገር ፍሪኤል የተሰኘ የጣሊያን ኩባንያ ጥጥ ለማምረት ወደአካባቢው በግብርና ኢንቨስትመንት የተሰማራ ቢሆንም ከጊዜ ወደጊዜ ባጋጠመው ችግር የተነሳ ቴክኖሎጂ ሲቀያይር ቆይቶ በመጨረሻ የሶላር ፓምፕ በመጠቀም በ axial-flow pump ውሃ ከኦሞ ወንዝ በመጥለፍ የሙዝ እርሻ የጀመረ ሲሆን ከዚህ

ልምድ በመነሳት ከፊል ግብርና መጀመር ለሚፈልጉ የአካባቢው አርሶ አደሮች ጥሩ ልምድ የሚገኝበት በመሆኑ መንግስት በቀላል ወጪ የመስኖ ስራን ማስፋፋት እንደሚችል ሰፊ ተሞክሮ የሚሰጥ ሆኖ አግኝተነዋል። በተጨማሪም የኦሞራቴ ከተማ አስተዳደር ከደቡብ ውሃ ስራዎች ጋር በመተባበር በከተማው ምዕራብ በኩል የኦሞን ውሃ ለመጥለፍ የናፍጣ ጀኔሬተር በመጠቀም የብረት ቧንቧ ፓምፖችን ለመግጠም ጥረት እያደረገ ቢሆንም በመለዋወጫ እጥረትና ጀኔሬተሩ ከሚጠቀመው የናፍጣ ፍጆታ አንጻር አዋጭ ስላልሆነ ይህን ልምድ መጠቀም ይችላል ብለን እናምናለን። እዚህ ላይ ለማስታወስ የምንፈልገዉ የጊቤ-3 የሃይል ማመንጫ በሚገነባበት ወቅት ከአካባቢ ተጽዕኖ አኳያ የአርብቶአደር ማህበረሰብ የወንዝ ሙላት ሸሽ መስኖ ልማት የሚቋረጥ በመሆኑ ዘመናዊ መስኖ በመንግስት እንደሚሰራለት የተገባዉ ቃል ተግባራዊ ቢደረግ መልካም እንደሚሆን ነዉ። ከዚህ አንጻር የሚመለከተዉ የዉሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴርም ይህን ሥራ ማስጀመር እንዳለበት ሃሳብ እናቀርባለን።

ከመንገድ ትስስር አኳያ ከቱርሚ ወደኦሞራቴ ደረጃዉን የጠበቀ መንገድ ተሰርቶ አገልግሎት ላይ ዉሏል። ይሁን እንጂ ከቱርሚ ቀይአፈር እንዲሁም ከቱርሚ ወይጦ የሚያገናኙ መንገዶች እንደሚሰሩ ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም መንገዶቹ እስካሁን ሳይሰሩ መቆየታቸዉ በአካባቢዉ የቱሪስት ፍሰትም ሆነ ሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ችግር እንደፈጠረ የተገነዘብን በመሆኑ የሚመለከታቸዉ አካላት ክትትል አድርገው መንገዱ እንዲሰራ እንመክራለን። ከቱርሚ በኩል እስከኦሞራቴ ከተማ የዘለቀዉ መንገድ ከኦሞ ብሔራዊ ፓርክና ከኦሞ ኩራዝ ስኳር ፕሮጀክቶች ጋር ለመገናኘት አጭር ርቀት ያለዉ ቢሆንም የኦሞ ፓሊዮንቶሎጂ ሳይት በኩል የሚያልፍ ሆኖ በመገኘቱ 11 ኪሜ ሲቀረው መንገዱ በመቆሙ 60 ኪሜ ብቻ የነበረውን ርቀት ከ400 ኪሜ በላይ ዙሪያ ጥምጥም እንዲኼድ ስላደረገው አማራጭ ዲዛይን ተሰርቶ መንገዱ እንዲጠናቀቅ ምክረሃሳባችንን እናቀርባለን። በነዚህ አካባቢዎች ከግብርና ኢንቨስትመንት ጋር ተያይዞ ትኩረት የሚሻ ጉዳይም ሰፊ እንደሆነ ታዝበናል። በአካባቢዉ የተሰማሩ አንዳንድ የግብርና ባለሀብቶች ጥሩ የሚንቀሳቀሱና ሙዝ ኤክስፖርት ማድረግ የጀመሩ፤ እንዲሁም በሶላር የሚሰራ ወጪ ቆጣቢ መስኖ ማስተዋወቅ በመጀመራቸዉ ልምዱን ለማስፋት አስተዋጾ ማበርከት የቻሉ የመኖራቸዉን ያህል መሬት ወስደዉ ሳያለሙ የቀሩትንም ለመታዘብ ችለናል። በካሮ አካባቢ ከኦሞ ወንዝ ዳርቻ የካሮ ማህበረሰብ በባህላዊ መንገድ ቀፎ ሰቅሎ ማር በማምረት እንዲሁም ሌሎች የኢኮስስተም አገልግሎትና ምርቶችን በማግኘት ኑሮዉን በሰፊዉ ሲደግፍበት እንደነበረ የሚነገረዉን የወንዝ ዳርቻ ጥቅጥቅ ያለ ደን በመመንጠር 30,000 ሄክታር መሬት ከመነጠረ በኋላ የዉሃ መሳቢያ መስመር ብቻ ዘርግቶ ጥሎ የጠፋ ኤልሴ የሚባል የቱርክ ኩባንያ እንደነበር ለመታዘብ ችለናል። አርብቶአደሩም ወይ ልማቱ አልለማ፤ ወይ ደናችን አልተረፈልን በሚል

ቁጭቱን ሲገልጽልን አስተዉለናል። በተመሳሳይ በማጎ ፓርክ አካባቢም አይካኦዲስ የተሰኘ ኩባንያ 10,000 ሄ/ር ከፓርኩ አካል ተቆርጦ ተሰጥቶት ሲያበቃ አንዳች ልማት ሳያከናዉን እንደቀረ በማጎ ፓርክ ጉብኝታችን ወቅት አመራሩ ቅሬታዉን ሲገልጽ ሰምተናል።

በጥቅሉ ሲታይ በነዚህ አካባቢዎች ከመንግስት ጥረት ባሻገር የግል ባለሀብቱ ባግባቡ ቢሰማራ እጅግ ሰፊና ኢትዮጵያን ጭምር መቀለብ የሚያስችል ምቹ መሬትና ዉኃ እያለ በአካባቢዉ የሚሰማሩ የግብርና ባለሃብቶች ከጥቂቶች በስተቀር አፈጻጸማቸዉ እጅግ ደካማና ደን መንጥረዉ የሚጠፉ በመሆኑ በአንድ በኩል አርብቶአደሩን በአዉትግሮወርነት በማስተሳሰር እንዲሁም የግብርና ሥራ ዕዉቀትና ክህሎት ሽግግር ለማፋጠን ጉልህ አስተዋጽዖ ሊያደርጉ የሚችሉበት፤ በሌላ በኩል ባካባቢዉ ያለዉን ሰፊና ለም የመስኖ መሬት ተጠቅመዉ ከፍተኛ ምርት ቢያመርቱ ኖሮ አገራዊ የምግብ ችግራችንን መቅረፍ የሚቻልበት ዕድል ሰፊ ቢሆንም ሁለቱን ግቦች የሚያሳካ ሥራ መሬት ላይ አይታይም። ስለሆነም፤ በተለይም በግብርና ኢንቨስትመን ወደአካባቢዉ የሚሰማሩ ሃይሎች ላይ ከላይ እስከታች ልዩ ክትትልና ተጨማሪ ድጋፎች እንደሚያስፈልጉ ለማሳሰብ እንወዳለን።

በተጨማሪም በአካባቢው ሰባት የሚሆኑ የእርሻ ኢንቨስትመንት ያላቸው ድርጅቶች ያሉ ሲሆን የካሣ ክፍያ ያልተፈጸመላቸው በመሆኑ በአፋጣኝ እንዲፈጸምላቸው እንመክራለን። ተጠቃሎ ሲታይ የሀመርና ካሮ ብሄረሰቦች በጎርፍ ማቀብና በጥልቅ ጉድጓድ ዉሃ እንዲሁም የዳሰነችና የኛንጋቶም ብሄረሰቦች የኦሞ ወንዝ ዉሃን ማዕከል ያደረገ ጥምር ግብርና ከቱሪዝም ልማቱ ጋር አቀናጅተዉ የሚበለጽጉበት የተቀናጀ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ርብርብ እንዲደረግ ምክራችንን እናቀርባለን።

## 4.2 በኦሞ ብሔራዊ ፓርክ በተደረገ ጉብኝት የታዩ እዉነታዎች፤ ችግሮች፤ የተቀመጡ መፍትሄዎችና ምክረሃሳቦች

የኦሞ ብሄራዊ ፓርክ በዞኑ በስተደቡብ ምዕራብ ከጂንካ በ140 ኪ.ሜትር ርቀት የሚገኝና በዩኔስኮ ሚሽን ድጋፍ ከተቋቋሙ የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ብርቅዬ ብሄራዊ ፓርኮች አንዱ ነዉ። ፓርኩ ከተቋቋመበት 1958 ዓ.ም (እንደኢ.ት/ አቆጣጠር) ጀምሮ የተለያዩ አካላት ያስተዳደሩት ሲሆን የገበያ ሞዴል ተብሎ የሚታወቀዉና በእዉቁ የአፍሪካን ፓርክስ ኩባንያ በግል እንዲተዳደር እስከተፈቀደበት 2005 (እ.ኤ.አ) ድረስ የመጀመሪያዎቹን 2 ዓመታት በእንግሊዛዊዉ ሊ.ብራዉን ሲተዳደር ቆይቶ በሁዋላ መንግስት በሚመድባቸዉ የፓርክ ዋርደኖችና ሬንጀሮች ለረዥም ጊዜ ሲመራ እንደቆየ ከፓርኩ ሃላፊዎች ገለጻ ለመረዳት ችለናል።

ፓርኩ በሀገራችን በብዝሃ ህይወት ሀብቱና በስፋቱ እጅግ አመርቂ ቢሆንም ምንም ዓይነት መሰረተልማት ያልተዘረጋለት በመሆኑ ተደራሽ ሳይሆንና በቂ ቱሪስት ለመሳብ ሳይችል ከሩቅ እየተናፈቀ ከመቆየቱም በላይ ባለቤት አልባ እስኪመስል ድረስ እጅግ አሳዛኝ የሚባሉ ጉዳቶችንም ሲያስተናግድ የቆየ ፓርክ ነዉ። ፓርኩ 4068 ካሬ ኪ.ሜትር የሚሸፍን የቆዳ ስፋት ያለዉና በወንዛማ ደኖች፤ በቁጥቋጦዎች፤ እንዲሁም እጅግ ሰፊዉን ሜዳማ አካል በሚሸፍንና ለዓይን በሚማርክ፤ ለእይታ በሚታክት ሳር የተሸፈነ ሲሆን በዚሁ ታይቶ በማያልቅ ሳራማ ምድር በርካታ የዉድምቢ፤ የዝሆን፤ ጎሽ፤ አንበሳ፤ ነብር፤ ቆርኪ፤ አምበራይሌ፤ እና ሰጎንን ጨምሮ በርካታ የአዕዋፍ ዝርያዎች የሚገኙበት ሲሆን እነዚህን ብርቅዬ እንስሳት በየመንጋቸዉ ከቅርብ ርቀት ለማየት የሚያስችል ልዩ መስህብ ያለዉ ፓርክ ነዉ። ይህን ፓርክ ለየት የሚያደርገዉ በሃገር ዉስጥ እስከ ጨበራ ጩርጩራ ፓርክ የሚዘልቅ የግንኙነት መስመር መኖሩ ሲሆን ከደቡብ ሱዳን ቦማ ፓርክ ጋር ባለዉ ግንኙነት ዝሆኖች ድንበር ሳይገድባቸዉ ወቅት እያፈራረቁ የሚመላለሱበት ረዥም ኮሪደር ያለዉ መሆኑ ነዉ። የሀገራችን ፓርኮች እስከቅርብ ጊዜ ድረስ አንዳች የረባ የመንግስት ትኩረት ሳያገኙ የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣንም በተለያዩ ወቅቶች ከግብርና መ/ቤት ጋር እየተለጠፈ በሰዉ ሃይልም ሆነ በበጀት ፓርኮቹን ለማስጠበቅ የሚያበቃ ቁመናና አቅም ሳይኖረዉ እንደቀየ ይታወሳል። የፓርክ ብዝሀ ህይወትም ለአካባቢዉ ማህበረሰብ አማራጭ የኑሮ መሰረት ባለመመቻቸቱ ለከፋ ጉዳት ሲጋለጥ በመቆየቱ የፓርክ አስተዳደርን ለማዘመን ታስቦ የነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክና ቀጥሎም የኦሞና ጋምቤላ ብሄራዊ ፓርኮችን በገበያ ሞዴል በግል እንዲያስተዳድር ዉል የተሰጠዉ የአፍሪካን ፓርክስ የተሰኘ የደች ኩባንያ ብዙም ሳይቆይና ሳይሳካለት በአካባቢዉ ማህበረሰብ ግፊትና ጥቃት ሳቢያ ጥሎ መዉጣቱ ሌላዉ ችግር ነዉ። የኦሞ ብ/ፓርክም በዚሁ ኩባንያ እንዲተዳደር ስምምነት ተደርሶ በ2005 (እ.ኤ.አ) ሥራዉን ከጀመረ በኋላ በአካባቢዉ ማህበረሰብ በተለይም ሱርማዎች በደረሰበት ጥቃትና የመሰረተልማት አለመኖር ሳቢያ ከሦስት ዓመታት ቆይታ በሁዋላ ጥሎ እንደወጣና ፓርኩ በኢዱልጥባ እጅ እንዲተዳደር ግድ የሆነበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ፓርኩ የረባ የመንገድ አዉታር ሳይኖረዉ የቆየና በየዓመቱ በጣት የሚቆጠሩ ጎብኝዎችና ተመራማሪዎች የሚጎበኙት ሆኖ ቢሰነብትም በአካባቢዉ የስኳር ፋብሪካ ለመክፈት በመንግስት ደረጃ ከተወሰነ በሁዋላ አሳዛኝም አስደሳችም ክስተቶችን ያስተናገደበት ሁኔታ ታይቷል።

የኦሞ ኩራዝ ስኳር ልማት በአካባቢዉ ሲጀመር በቂ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሳይካሄድና የይድረስ ይደረስ የተደረገዉ ጥናትም ቢሆን በወጉ ተግባራዊ ሳይደረግ በመቅረቱ በፓርኩ ብዝሃህይወት ላይ ሰፊ የሚባል ጉዳት ያስከተለበት ሁኔታ ታይቷል። በአንድ በኩል የእንስሳቱን መኖሪያና መዋያ አካባቢን በመረበሽ በእንቅስቃሴያቸዉና አኗኗራቸዉ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ሲሆን በሌላ በኩል አካባቢዉን ለተለያዩ ብክለቶች ማለትም የድምጽ፤ የጭስ (ከተሽከርካሪ፤ ከፋብሪካ፤ እንዲሁም ከሸንኮራ አገዳ ቃጠሎ) እና የባዕድ ዕጽዋት

መስፋፋት (ለአቀንጭራና መሰል መጤ ወራሪ አረሞች) የዳረገበት ሁኔታ የሚጠቀስ ነዉ። በአንጻሩ ደግሞ ፈረንጆቹ blessing in disguise እንደሚሉት ፋብሪካዉ በአካባቢዉ በመከፈቱ ምክንያት ምንም ዓይነት የመንገድ ተደራሽነት ያልነበረዉ ይኅዉ ፓርክ መጠነ ሰፊ የሆነ አስፋልትና ክረምት ከበጋ የሚያገለግሉ መንገዶች ተሰርተዉለት የተደራሽነት ችግሩ በእጅጉ የተቀረፈበትና ምናልባትም ፋብሪካዉ ባይሰራ ኖሮ ወደፊት በረዥም ዓመታትም ቢሆን ያን ያክል መንገድ በአካባቢዉ ይሰራል ብሎ መገመት በሚያዳግት አኳኋን የመንገድ ችግርን ያቃለለበትን ሁኔታ በአዎንታነት ተመልክተናል።

በፋብሪካዉ ምክያት በፓርኩ ላይ እየደረሰ ያለዉን ጉዳት ለመቀነስና ፓርኩን ከጥፋት ለማዳን ከዚህ ቀደም በኢዱልጥባና በፋብሪካዉ ሃላፊዎች ተደጋጋሚ ጥረቶች ተደርገዉ በቅርቡ ከጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት የተላከ ቡድን ዝርዝር ጥናት አካሂዶ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን እንዳስቀመጠ በጉብኝቱ ወቅት ከሁለቱም ወገን በተሰጠዉ ማብራሪያ ለመረዳት ችለናል። ይሁንና በኛ እይታ ፋብሪካዉ በፓርኩ ብዝሃ ህይወት ጥበቃ ላይ ያደረሳቸዉ ተጽዕኖች ምንድናቸዉ፤ ፓርኩም ሆነ ስኳር ልማቱ የጋራ ሀብቶቻችን በመሆናቸዉ ያለፈዉ አልፎ ካሁን በኋላ ግን ጉዳት በመቀነስ ልማቶቹ ታርቀዉ የሚቀጥሉበት አስማሚ አማራጮች ምን ሊሆኑ ይገባል በሚሉ ነጥቦች ዙሪያ ሁለቱን ወገን በማወያየት አዋጭና ሊተገበር የሚችል የጋራ መፍትሄ ለማስቀመጥ ጥረት አድርገናል። በመፍትሄ ሃሳቦቹም ላይ የጋራ ርብርብ ለማድረግም ስምምነት ተደርሷል። በዚሁ መሰረትም ፓርኩን በዘላቂነት በነጋሪት ጋዜጣ ለማካለል የተጀመረዉ ሥራ በሚንስትሮች ም/ቤት በቅርቡ ዉሳኔ ያገኛል ብለን እንጠብቃለን።

የተከሰቱ ችግሮች ሲዘረዘሩና ፋብሪካዉ በፓርኩ ላይ ያደረሳቸዉን ጉዳቶች ስንመለከት፤የኦሞ ኩራዝ ስኳር ፕሮጀክት የካናል ግንባታ ለወትሮው የሚዳ አህዮች፥ ሳላዎች፥ ጎሾችና ዝሆኖች ሳር የሚግጡበትን ሜዳ ለሁለት የከፈለው በመሆኑ የዱር እንስሳቱ ፓርኩን እየለቀቁ እንዲሄዱ ይልቁንም በጎረቤት ሃገር ደቡብ ሱዳን ወደሚገኘው ቦማ ፓርክ እንዲሰደዱ እያስገደደ ይገኛል። በተጨማሪም ካናሉን ለመቆፈር አገልግሎት የሚውሉት ከባድ ተሽከርካሪዎች በማረሻ መሳሪያዎቻቸው እና ጎማቸው ይዘዋቸው የገቡ ባዕድ አረሞች የአካባቢውን ተክሎችና ሳሮች እያጠቁ እንደሚገኙ ታዝበናል።

በአንዳንድ የፓርኩ አካባቢዎች የተቆፈረው ካናል እንደዝሆን ያሉ የዱር እንስሳት በቀላሉ ከቦታ ቦታ ማለፍ እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። ስለሆነም የኦሞ ኩራዝ 3 የሸንኮራ ልማት ቦታ እንዲሆን ታስቦ የነበረው ከኩማ እና ካኩ ወንዝ መገናኛ ጀምሮ ያለው 7500 ሄክታር መሬት (ከሙኢ ወንዝ ወደፋብሪካዉ 5 ኪ/ሜትር) የዱር እንስሳቱ በይበልጥም የዝሆኖች መንቀሳቀሻ በመሆኑ በስኳር ኮርፖሬሽን፥ በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ

ባለስልጣን እና በኃይለማርያም እና ሮማን ፋዉንዴሽን መካከል በተደረገ ጥልቅ ውይይት ጥቅም ላይ እንዳይውልና በምትኩ ከሌላ አጎራባች ከሚገኝና እንስሳቱ ከማይገኙበትና ከማይንቀሳቀሱበት ስፍራ እንዲተካ ስምምነት ተደርሷል። ከዋና ካናል በተጨማሪም የፕራይመሪ ካናል ዝርጋታዉ ይህንን ታሳቢ በማድረግ ተጨማሪ ርዝመት የሚያስከትል ቢሆንም ይህን ስምምነት የሚያሳካ የዲዛይን ለውጥ እንዲደረግና በተጨማሪ ከኦሞ ወንዝ ጀምሮ 2 ኪሜ የሚሆን የወንዝ ለወንዝ ጫካ እንዳይነካ እንዲሁም በሚገነባው ካናል ግራና ቀኝ ለቅኝት የሚረዳ መንገድ በስኳር ኮርፖሬሽን እንዲገነባ ከስምምነት ተደርሷል። በአካባቢዉ በስፋት እየተዛመተ ያለዉ ወራሪ አረም (invasive alien species) ከቁጥጥር ዉጪ በመሆን ተፈጥሮአዊዉን የፓርኩን ስነምህዳር ለከፋ ጉዳት ከመዳረጉ በፊት የስኳር ፋብሪካዉን ሰራተኞችንና የአካባቢዉን ማህበረሰብ በማስተባበርና የጉልበት ክፍያ በመፈጸም በእጅ የማጽዳት (ማስነቀልና ማቃጠል) ሥራ በቀጣይነት በፋብሪካዉ አማካይነት እንዲሰራ ከመግባባት ላይ ተደርሷል። የዱር እንስሳቱ በተለይም ዝሆኖች ዋናዉን ካናል ተሻግረዉ ማለፍ ያለባቸዉ በመሆኑ ይህንን ለማሳለጥ የተሰራዉ ዲዛይን መልካም በመሆኑ ወደግንባታ ፈጥኖ እንዲገባ ምክራችንን እንለግሳለን።

ከስኳር ፋብሪካዉ አካባቢያዊ ተጽዕኖ ባሻገር ይህ ፓርክ በርከት ያሉ ሌሎች ችግሮችም የተደቀኑበት ፓርክ ሆኖ አግኝተነዋል። በመሰረተልማት ረገድ በስኳር ፋብሪካዉ ምክንያት መንገድ ባይሰራለት ኖሮ ማንም ደርሶ ሊያየዉ እንደማይችል እሙን ነዉ። የፓርክ ሰራተኞች መኖሪያና መስሪያ ካምፕ እንኳን ያኔ በምስረታዉ ጊዜ ማለትም በ1958 እንግሊዞች በሰሩትና የኋላ ደግሞ አፍሪካን ፓርክስ ኩባንያ እድሳትና ማስፋፊያ ከሰራዉ (ባብዛኛዉ በአካባቢዉ ማህበረሰብ የፈረሱ ባንጋሎዎች ይታያሉ) በስተቀር በመንግስት በኩል የረባ ትኩረት ያገኘበት ሁኔታ አይታይም። የፓርክ ሃላፊዎችና ሬንጀሮች እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ዉስጥ ኑሯቸዉን እንደሚገፉና የግል ህይወታቸዉም ቢሆን በአደጋ ዉስጥ ያለ መሆኑን ታዝበናል።

በአካባቢዉ የሚገኘዉና በሱዳን ድንበር በቶፖሳ ማህበረሰብ ተገፍቶ ብዙ ኪ.ሜትሮችን ወደፓርኩ ለመሸሽ የተገደደዉ የሱርማ ማህበረሰብ እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ኑሮዉን ለመግፋት ስለተገደደ የፓርኩን እንስሳት በማደንና ለእንስሳቱ ግጦሽ ሲል ፓርኩን በማቃጠል ከሚያደርሰዉ ጫና ባሻገር የታጠቀ ሃይል በመሆኑ በአንድ በኩል በአጎራባች ከሚገኘዉ የኛንጋቶም ማህበረሰብ ጋር በተደጋጋሚ ለግጭት በመዳረግ ፓርኩን የግጭት ቀጣና ሲያደርገዉ፤ በሌላ በኩል በተገቢዉ ያልታጠቁትን የፓርኩን ጠባቂዎች በየጊዜዉ ተኩሶ በመግደል ፓርኩን ለመጠበቅ ለተሰማሩ ሃይሎች ከፍተኛ ስጋት ደቅኖ ይታያል። የሱርማዉ ቁጡና ሃይለኛ መሆን ምንም እንኳ ጥልቅ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም በዋናነት አሁን ያለዉ አረዳድ በድንበር አካባቢ ካለዉ ያልተረጋጋ የጸጥታ ሁኔታ በተለይም ከቶፖሳ በደረሰበት መገፋት ምክያት ሲሆን በተራዉ ሱርማም የዲዚን ማህበረሰብ

እየገፋ ከታች በኩል ከኛንጋቶምም ጋር የተካረረ ቁርሾ ዉስጥ የገባበት ሁኔታ አንደኛዉ መነሻ ሲሆን በተወሰነ መልኩም ቢሆን በዲዚና በኛንጋቶም አካባቢዎች በተደራጀ መንገድ የላይብሊሁድ ድጋፍ ለማድረግ የተሞከረዉ ሥራ በነርሱ ዘንድ አለመሰራቱ ሌላዉ ምክንያት ነዉ። ሱርማን አይቶ የመበርገግ ዝንባሌም ጎልቶ ስለሚታይ ይህ ነዉ የሚባል የኑሮ ጥያቄዎቻቸዉን ለመመለስ የተሞከረ ነገር ባለመኖሩ እየከፋ የመጣ ባህሪይ እንደሆነ ለመረዳት ችለናል።

በኩራዝ ቁጥር ሶስት ስኳር ፋብሪካ በኩል የተወሰኑ ጥረቶች ተደርገዉ በፋብሪካዉ የጥበቃና ሌሎች ሥራዎችም ላይ ለማሰማራት የተደረጉ ዉስን ጥረቶች ጥሩ ቢሆኑም ጎላ ባለ መልኩ የማህበረሰቡን መሰረታዊ የሆኑ ጸጥታ ችግር የወለዳቸዉና መሰረታዊ የኑሮ ጥያቄዎች የሆኑትን ጉዳዮች ለመመለስ የሚያስችል የተቀናጀ የመንግሰት አካላት ጥረት ብዙም አይታይም። ከዚህ አኳያ ቦዲንና ኛንጋቶሙን ለማረጋጋት በዋናነት በስኳር ፋብሪካዉ የተጀመሩ ዉጤታማ ጅምሮች በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እገዛ ታክሎ በሱርማዉም ዘንድ ቢከናወን፤ በተለይም ደግሞ የጸጥታ ሥራዉ ከዋናዉ ገፊ ምክንያት (ከቶፖሳ ጋር ተያይዞ ያለዉን) በመፍታት የሚጀምር ቢሆን ለዉጥ ተያይዞ ሊመጣ እንደሚችል እናምናለን።

የእነዚህን ሰዎች መሰረታዊ የኑሮ ጥያቄዎቻቸዉን ለመመለስ ቢቻል ሊረጋጉ እንደሚችሉና በፓርኩ ብዝሃ ህይወት ላይ ያላቸዉን ጥገኝነትም ሆነ የሪሶርስ ፍላጎቱ በሚፈጥረዉ ግጭት የሚታየዉን አመለኝነታቸዉን ማረቅ እንደሚቻል ሌላዉ ማሳያ ከሰል ማክሰልና  ዓሳ አስግረዉ መሸጥ መጀመራቸዉ ነዉ፡፤ በአካባቢዉ የሚሰሩ የቻይና ዜጎችና ሌሎች ህገወጦች በርከት ያለ ወጥመድ በስዉር አቅርበዉላቸዉ እንስሳትን አጥምደዉ እስከመሸጥ ደርሰዉ ታይተዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ የማያቋርጥ ገቢ ማግኛ አማራጭ ስልቶች ተነድፈዉ በባላባቶቻቸዉ አማካይነት መረጋጋትን በማለማመድ ወደሥራ እንዲገቡ ቢደረግና ከፓርኩ ብዝሃ ህይወትም ዘላቂና ጉዳት በማያስከትል መንገድ የኢኮሲስተም ዉጤቶችና አገልግሎቶች (ecosystem goods and services) ተጠቃሚ ማድረግ ቢጀመር የማይቀየሩበት ምንም ምክንያት የለም።

በዳሰነች፤ በቦዲና በኛንጋቶም እንደተሞከረዉ የከፊል ግብርና ሥራን በማለማመድ፤ በተለይም ደግሞ በመስኖ ዳርቻዎች ለይቶ በማስፈር በአዉትግሮወርነት ሸንኮራ አምርተዉ ለፋብሪካ እንዲያቀርቡ የሥኳር ፋብሪካ ሃላፊዎች በዕቅዳቸዉ አካተዉ በትኩረት መሥራት እንደሚገባቸዉ ከስምምነት ተደርሷል። ይሁንና ይህ ሥራ ለፋብሪካዉ ብቻ የሚተዉ ባለመሆኑ የዞኑም ሆነ የክልል አርብቶአደር ቢሮ በከፍተኛ ትኩረት በጋራ አቅደዉ

የሱርማን ጉዳይ በአካባቢዉ ቁልፍ የጸጥታና የልማት ጥያቄ አድርገዉ በመያዝ ሊሰሩት እንደሚገባ እምነታችን ነዉ።

ከጸጥታ አኳያም ድንበር ተሻግረዉ የሚመጡትን ቶፖሳዎች ወደአገራቸዉ መመለስ እንዲሁም ተመልሰዉ እንዳይመጡ ዘላቂ የጥበቃ ፖስት መስራት አስፈላጊነቱ የጎላ ነዉ። በተመሳሳይ መልኩ ኛንጋቶሞች በኬንያ የሚገኘዉ ቱርካና ማህበረሰብ በሚያደርስባቸዉ ጥቃት ምክንያት ወደፓርኩና ወደሱርማዎች የሚዘምቱ በመሆኑ በተመሳሳይ በኬንያ በኩልም በፌዴራል መንግስት የተደራጀ የጥበቃ ፖስት እንዲቋቋም ማድረግ አማራጭ የሌለዉ ሆኖ አግኝተነዋል።

በጥቅሉ ሲታይ፤ የኦሞ ብሄራዊ ፓርክ በሀገራችን እጅጉን ዉብና የደለበ የተፈጥሮ ሃብት የያዘ፤ በተገቢዉ መንገድ ከለማ አገራችን ከቱሪዝም ገቢዉ የላቀ ጥቅም ለማግኘት የጣለችዉን ግብ ለማሳካት የአንበሳዉን ድርሻ መጫወት የሚችል፤ ምናልባትም እንደ ደቡብ አፍሪካዉ ታላቁ ክሩገር፤ እንደሞዛምቢኩ ጎሮንጎሳ፤ እንደኬንያዉ ማሳይ ማራ፤ እንደታንዛኒያዉ ሰሬንጌቲ ፓርኮች የዓለም ትኩረት በመሳብ ባጭር ጊዜ ዉስጥ የቱሪስቶች ምርጥና ታዋቂ መዳረሻ በመሆን የአገራችንን ገጽታም ሆነ የአካባቢዉ አርብቶአደሮችን ህይወት ለመቀየር የሚያስችል አስደማሚ ሀብት መሆኑን መንግሰትና ባለድርሻ አካላት በአንክሮ ተረድተዉ ሊንቀሳቀስሱ ይገባል እንላለን። ይህ ሥራ ለኢዱልጥባ ብቻ የሚተዉ ጨርሶ ሊሆን አይገባም። ኦሞንና ማጎን እንዲሁም ጨበራጩርጩራንና ጋምቤላ ብሄራዊ ፓርኮችን ጠጋ ብሎ የተመለከተ ማንኛዉም የልማት ሃይል ሃገራችን ምን ዓይነት ታኣምራዊ ሃብት እንዳላት መገንዘብ ብቻ ሳይሆን ይህንኑ ሃብት በዘላቂነት የማልማት ጉዳይ በአንድ ተቋም ጫንቃ ላይ ሊንጠለጠል እንደማይችልና እንደማይገባም በአግባቡ ሊረዳዉ እንደሚችል ከራሳችን የመስክ ጉዞ ልምድ መዉሰድ ይቻላል እንላለን። ምክንያቱም ሀብቱም ሆነ ሀብቱን የተጫጫነዉ ፈተና ከአንድ ትኩረት ተነፍጎት ዘመናትን ካስቆጠረ ተቋም አቅም እጅጉን የገዘፈ ነዉና።

ከመንገድ አኳያ ከላይ እንደተገለጸዉ ከስኳር ፋብሪካ ጋር ተያይዞ የተሰራዉ መንገድ ትልቅ የግንኙነት ማነቆ የፈታ ቢሆንም አሁንም ያልተፈቱ ሌሎች ማነቆዎች አሉ። ዋናዉ ችግር ደግሞ ከኦሞ ማዶ ማለትም ከማጂ በኩል ያለዉ ነዉ። ከዚህ አንጻር ከሳዉላ ማጂ እንዲሰራ የተያዘዉ መንገድ ጥየራት ችግሩ እንደተጠበቀም እስከ ላሃ ከተማ ድረስ ከተሰራ በኋላ ወደማጂ ሊቀጥል አልቻለም። በኦሞ ወንዝ ላይ ድልድይ የተሰራ ቢሆንም ከላሃ እስከኦሞ እንዲሁም ከድልድዩ ማዶ እስከማጂ መንገዱ ባለመሰራቱ ተንጠልጥሎ ስለቀረ ከማጂ ጋር ለመገናኘት አስቸጋር ሁኔታ ይታያል። ይህ መንገድ ከወጪም አንጻር ብዙም ርቀት የሌለዉና ተፋጥኖ እንዲሰራ ቢደረግ በስኳር ፋብሪካዉ በኩል የተሰራዉን የመንገድ ኔትወርክ የተሟላ በማድረግና ከምዕራብ ኦሞ

ዞን ጋር ሊኖር የሚገባዉን ግንኙነት በማሳለጥ የልማትም ሆነ የጸጥታ ማነቆዎችን በተሟላ መልኩ ለመፍታት ወሳኝ አቅም ስለሚሆን ትኩረት እንዲሰጠዉ ሃሳባችንን ለማቅረብ እንወዳለን።

## 4.3 በማጎ ብሄራዊ ፓርክ በተደረገ ጉብኝት የታዩ እዉነታዎች፤ ችግሮች፤ የተቀመጡ መፍትሄዎችና ምክረሃሳቦች

የማጎ ብሄራዊ ፓርክ በደቡብ ኦሞ ዞን ከጂንካ ከተማ በስተ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በ34 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን በስፋቱም 2200 ስኩወር ኪ.ሜትር የሚሸፍን ነዉ። ፓርኩ በ1971 ዓ.ም የተቋቋመና በደቡብ ክልል መንግስት የሚተዳደር ሲሆን በዉስጡም ዝሆን፤ጎሽ፤፤ አንበሳ ፤አቦሸማኔ፤ ነብር፤ ተኩላ፤ድፌርሳ አምበራሌ፤ አጋዘን ድኩላና ከርከሮ እንዲሁም ለመጥፋት የተቃረቡ ቀጭኔ፤ ዞብራና የሜዳ አህያ የመሳሰሉ አጥቢ እንስሳትንና በርከት ያሉ የአዕዋፍ ዝርያዎችን ከመያዙም በላይ በዉስጡ ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ የኔሪና የማጎ ወንዞችን ተከትለዉ የበቀሉ የሪቨራይን ደኖች ለአጥቢ እንስሳቱ ምቹ መጠለያ የሚሰጡ ሲሆን ባብዛኛዉ ግን ቁጥቋጧማና ሳራማ ሆኖ በድንቅ የብዝሃ ህይወት ጸጋ የታደለ ነዉ።

ማጎ ብሄራዊ ፓርክ በስተምዕራብ የታማ እንስሳት መጠበቂያ፤ በስተደቡብ ደግሞ ከሙሪሌ የቁጥጥር አደን ክልል ጋር የሚዋሰን ሲሆን በዙሪያዉ የአሪ፤ የሙርሲ፤ የሃመር፤የካሮ፤ የበና፤ እና የኩይጉ፤ ብሄረሰቦች ይኖራሉ። በፓርኩ በተደረገዉ የ1 ቀን ጉብኝት የፋወንዴሽናችን የሥራ ሃላፊዎች፤ የብሄራዊ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን ቡድን፤የብሄራዊ ፓርኩ ሃላፊዎችና ሬንጀሮች፤ የወረዳና ዞን አመራሮች የተሳተፉ ሲሆን ስለፓርኩ አጠቃላይ ሁኔታ ዝርዝር መግለጫ ቀርቦ ዉይይት ተካሂዷል። በዚሁ ዉይይት ወቅት ከተነሱ ዋናዋና ነጥቦች ጎልተዉ የወጡት ችግሮች፤ አንደኛዉ በፓርኩ ዉስጥ ለዉስጥ የሚያስገባ የመንገድ መሰረተልማት አለመኖር ለጎብኝዎች አስቸጋሪ ሁኔታን የፈጠረ መሆኑ፤ በተለይም ፓርኩን አቋርጦ ወደካሮ ማህበረሰብ የሚያስወጣ 60 ኪ.ሜትር የሚገመት መንገድ ባለመጠገኑና ተመልሶ ጫካ በመልበሱ ከሀመር፤ ዳሰነች፤ ኛንጋቶምና ካሮ ጋር ሊኖር የሚገባዉን ግንኙነት ከ200 ኪ.ሜትር በላይ እንዲርቅ ማድረጉ ነዉ። በሁለተኛ ደረጃ የፓርኩ ይዞታ በዙሪያዉ ባሉ የሙርሲ ማህበረሰብ አባላት በስፋት እየተወረረና ወደመኖሪያ መንደርነት እየተቀየረ ያለ መሆኑ፤ እንደኦሞ ብ/ፓርክ ሁሉ እዚህም የጸጥታ ችግር በስፋት የሚታይ ሲሆን የፓርክ ሬንጀሮችና ወደፓርኩ ለስራ የመጡ ሰዎች ጭምር በሽፍታ የሚገደሉበት ሁኔታ ተደጋግሞ የሚታይ መሆኑ፤ የፓርኩ ዙሪያ ማህበረሰብ አባላትን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻልና በፓርኩ ሪሶርስ ላይ ያላቸዉን ጥገኝነት የሚቀንስ ትርጉም ያለዉ ሥራ አለመሰራቱ ሰፊ ተጽዕኖ መፍጠሩ በዉይይቱ ወቅት በአጽንኦት ተነስቷል።

የፓርክ ሬንጀሮችና ሃላፊዎች ፓርኩን ለማስጠበቅ የሚያስችል በቂና የተሟላ የደመወዝ፤ የፋሲሊቲና የደህንነት ዋስትና አለማግኘታቸዉ፤ በፓርኩ አካባቢ ንጹህ የመጠጥ ዉሃ ለመስራት የተጀመረዉ ሥራ እንኳ

ባለሙያዎች ጥቃት ደርሶባቸዉ መጠናቀቅ አለመቻሉ፤ የፓርኩ ነባር ብዝሃ ህይወት በአካባቢዉ በተስፋፋዉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ምክንያት በባዕድ ዕጽዋት ዝርያዎች በተለይም በአደገኛዉ የፓርቲኒዬም አረም መስፋፋት ምክንያት ለከፋ አደጋ የተጋለጠ መሆኑ፤ በፓርኩ ዉስጥ ከሚፈሱ ወንዞች ዋነኛ የሆነዉ የነሪ ወንዝ ከጂንካ ዩኒቨርሲቲ በሚለቀቅ መርዛማ ፈሳሽ ክፉኛ እየተበከለ በመሆኑ በአካባቢዉ አርብቶ አደርም ሆነ በእንስሳቱ ጤና ላይ ችግር የተጋረጠ መሆኑ ከተነሱ ችግሮች ዋናዋናዎቹ ናቸዉ።

በነዚህና በመሳሰሉ ተግዳሮቶች ላይ ዉይይት የተደረገ ሲሆን የተለያዩ አካላትም በመፍትሄዎቹ ላይ ድርሻ ድርሻቸዉን እንዲወስዱ ተደርጓል። በዚህም መሰረት  የመንገድ ችግር ለቱሪዝም ልማቱ ዋነኛ ማነቆ በመሆኑ ፋዉንዴሽናችንና የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን ከሚመለከታቸዉ የክልልና ፌዴራል አካላት ጋር በመነጋገር መፍትሔ እንዲገኝ መስራት እንዳለባቸዉና፤ የፓርኩ ዉስጥ ለዉስጥ መንገድ ብዙም ወጪ ሳይጠይቅ በጥርጊያ መልክ መሥራት የሚቻል በመሆኑ የክልልና የፌዴራል መንገዶች ባለሥልጣናት ትኩረት እንዲሰጡ እንዲደረግ ምክረሃሳባችንን እናቀርባለን።

የፓርክ ይዞታዉ በሙርሲ ማህበረሰብ የሚደርስበትን ወረራ ከመቀነስ አኳያ ሁሉም አካላት በቅንጅት መስራት እንደሚጠበቅባቸዉ ከስምምነት የተደረሰ ሲሆን በተለይም አረብቶአደሩ በፓርኩ ዉስጥ በሰፈረባቸዉ የመንገድ ዳርቻዎች አኗኗሩ ሲታይ ለቱሪስቶች በሚመች ቅርበት ተገኝቶ ፎቶግራፍ እየተነሳ ገቢ ለማግኘት ካለዉ ጠንካራ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ፍላጎት በመነሳት ደኑን ብዙም ሳይጨፈጭፍና ጠብቦ መንደር በመመስረት እንደሚኖር ለመረዳት ተችሏል። ከዚህም ባሻገር እንደአርሶአደር ማህበረሰብ ደን የማይጨፈጭፍና እርሻም የማይሰራ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በብዝሃ ህይወት ሃብቱ ላይ የሚኖረዉ ቀጣይ ተጽዕኖ ከራሱ ከሰፋሪዉ ብዛትም አንጻር ዉስን እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

ስለሆነም፤ ባሁኑ ሰዓት በፓርኩ ዉስጥ ባሉ የመንገድ ዳርቻዎች የሰፈሩና ራሳቸዉን በቱሪስት ፕሮዳክትነት በማቅረብ ኑሯቸዉን ለመግፋት የተገደዱትን ከፓርኩ ከማስወጣት ይልቅ ኢንቴግሬት በማድረግ የበለጠ በማደራጀት፤ በማሰልጠን፤ የፋይናንስና መሰል ፋሲሊቲዎችን በማቅረብ ሰዉነታቸዉን ብቻ ሳይሆን ለቱሪስት ገበያ የሚዉሉ ሌሎች የእጅስራና መሰል ምርቶችን እያመረቱ በዘላቂነት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ዕቅድ ነድፎ መስራት እንደሚገባ ከስምምነት የተደረሰ ሲሆን፤ ይህም በፋዉንዴሽናችን ዋና ዕቅድ ዉስጥ እንደሚካተትና የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን (ኢዱልጥባ)፤ የዞኑና የሚመለከታቸዉ የወረዳ አስተዳደር መዋቅሮች በቅንጅት እንደሚሰሩበት ከመግባበት ላይ ተደርሷል።

ይሁንና ከንግዲህ በተመሳሳይ መልኩ ወደፓርኩ ዉስጥ የሚደረግ ሰፈራ በዞኑ አስተዳደር አማካይነት እንዲገታና አርብቶአደሮቹ ባሉበት ሥፍራ ሆነዉ ከፓርኩ ከሚገኝ ገቢም ሆነ ከፓርኩ ኢኮሲስተም ሰርቪስስ ተጠቃሚ የሚሆንበት የላይቭሊሁድ ልማት ሥራ በትኩረት እንዲሰራና በዋናዉ ዕቅዳችን ዉስጥ እንደሚካተት መግባባት ላይ ተደርሷል። በዚህ ረገድ በክልሉ መንግስት የፓርክ ልማትና ጥበቃ አዋጅ መሰረት ከፓርኩ ከሚገኝ ገቢ 30 በመቶዉ ለማህበረሰብ ልማት እንዲዉል የተፈቀደዉን በጀት በሚመለከት በቀጥታ በፓርኩ ዙሪያ ያሉ ማህበረሰቦችን በማደራጀትና የላይቭሊሁድ ዕቅድ በመንደፍ ለዚሁ ተግባር በሚዉልበት መልኩ በኦሞ ማይክሮፋይናንስ በስማቸዉ እየተቀጠበ ዘላቂ የሆነ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት በማግኘት በቀጣይነት ኑሯቸዉን የማሻሻል ዓላማ ላይ እንዲዉል በዞኑ መንግስት በኩል ግልጽ አሰራር እንዲዘረጋ ከስምምነት ላይ ተደርሷል።

በፓርኩ በተደጋጋሚ የሚከሰተዉን የጸጥታ ችግር በተመለከተ የዞኑ አስተዳደር ሽፍቶችን አሳድዶ የመያዝና ለህግ የማቅረብ ሥራዉን አጠናክሮ እንደሚቀጥልና ለዘላቂ መረጋጋት እንዲረዳም በአካባቢዉ ትጥቅ ለማስፈታት ዝግጅት ማጠናቀቁን የገለጸ ሲሆን እነዚህ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረዉ እንደሚቀጥሉ በማረጋገጥ ሃላፊነት ወስዷል።

የፓርክ ሃላፊዎችና ሬንጀሮች ኑሮን ለማሻሻል በኢዱልጥባ በኩል ጥናት እንዲካሄድና አቅም በፈቀደ መልኩ ትኩረት እንዲሰጥ አስተያየት የተሰጠ ሲሆን የመጠጥ ዉሃን በሚመለከት የዞን አስተዳደር ከክልልና ከፌዴራል መንግስት ጋር በመተባበር ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ ከመግባባት ተደርሷል።

የጂንካ ዩኒቨርሲቲ የሚለቀዉ ቆሻሻና በካይ ፈሳሽ ለፓርኩ ብዝሃህይወትም ሆነ ለዙሪያዉ አርብቶአደር ህይወት አደጋን የሚደቅን በመሆኑ፤ ይልቁንም ዩኒቨርሲቲዉ በብዝሃህይወት ጥበቃ ላይ ከማንም በላይ ግንባርቀደምና አርአያነት ያለዉን የማህበረሰብ አገልግሎት ሚና መወጣት ሲገባዉ ጉዳት ማድረሱ ተገቢነት የሌለዉ መሆኑ ከግንዛቤ ገብቶ የዞኑ መንግስት ከዩኒቨርሲቲ አመራሮችና ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ፈጣን መፍትሄ እንዲበጅለት ከመግባባት ላይ ተደርሷል።

ባጠቃላይ በዚሁ ፓርክ በአደንና በሰፈራ አማካይነት እየተመናመነ የመጣዉን የእንስሳት ሃብት ከጥፋት በማዳን በፓርኩ ጠንካራ የቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲፈጠርና ከሚገኘዉም ገቢ ብረተሰቡ በቀጣይነት እየተጠቀመ ፓርኩን እንደግል ሃብቱ የሚጠብቅ የአርብቶአደር ማህበረሰብ የመፍጠር ግብ ያለዉ ሥራ በሁሉም አካላት ቅንጅትና ርብርብ መከናወን እንደላበት፤ ለዚህም መሰረተልማትና የጸጥታ ሥራዎች ልዩና ፈጣን ትኩረት

እንዲያገኙ ሆኖ በዋናነት ግን ሁሉም ሥራ የአካባቢዉን አርብቶአደር ማህረሰብ ህይወት መለወጥን ማዕከል አድርጎ የሚፈጸምበት አቅጣጫን ተከትሎ መስራት እንደሚገባ ግንዛቤ ተይዟል። በዚሁ ሥራ ፋዉንዴሽናችን የማህረሰብ አቅም በመገንባትና ለላይቭሊሁድ ልማት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት በመስራት ኮሪደሩ ሰፊ የቱሪስት ገበያ የሚፈጠርበት እንዲሆን በቁርጠኝነት እንደሚሰራም ለአካባቢዉ ማህበረሰብ ተወካዮች በዚሁ አጋጣሚ አረጋግጧል። ቱሪዝም ኢትዮጵያም በአካበቢዉ የቱር ገበያ እንዲስፋፋ ከአካባቢዉ የመንግስት መዋቅር ጋር ተቀራርቦ እንዲሰራና የተሟላ የቱሪስት ገበያ ፓኬጅ ቀርጾ እንዲተገብር አትኩሮት ሊሰጥ እንደሚገባ አስተያየት ቀርቧል።

## 5. ማጠቃለያ

የሃይለማሪያምና ሮማን ፋዉንዴሽን በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት አስተዋጽኦ ለማበርከት በመረጣቸዉ ብሄራዊ ፓርኮች እየታየ ያለዉን የአየር ንብረት ለዉጥ ተጽዕኖና በሰዉ ሰራሽ ችግሮች ምክንያት እየደረሰ ያለዉን የብዝሃ ህይወት መራቆት ለማስቆም ዋናዉ ሥራ መሆን ያለበት የብዝሃህይወት ጥበቃ ስራዉ የአካባቢ ማህበረሰብን የኑሮ ጥያቄዎችን በተገቢዉ በሚመልስና እነሱን በሚያሳትፍ አኳኋን ሲከናወን ብቻ መሆኑን በጥብቅ በመገንዘብ በዚህ ረገድ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት በተለይም በየደረጃዉ ካሉ የመንግስት አካላት ጋር ተባብሮ ለመስራት እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። ይህ ሥራ ዋናዉ ግቡ የአካባቢ ህብረተሰብን የብዝሃ ህይወት ስነምህዳሩ አካል አድርጎ በማየትና የብዝሃ ህይወት ጥበቃ ስራዉ የማህበረሰቡን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኑሮ በማሻሻል እንዲሁም የፓርኮቻችን የመጎብኘት አቅም በማሳደግ ከኢኮቱሪዝምና ከአማራጭ የገቢ ማግኛ ስልቶች ኑሯቸዉን በመደጎም በብዝሃ ህይወቱ ላይ ተገደዉ የሚያደርሱትን ጥፋት በመቀነስና ይልቁንም ዘላቂ ጥቅማቸዉ ከፓርኩና በፓርኩ ምክንያት እስከተጠበቀላቸዉ ድረስ ዋናዉ ጠባቂና ተንከባካቢ (principal conservation agents) ሃይሎች ሆነዉ የባለቤትነት ስሜት እንዲያዳብሩ ማድረግ ነዉ። ፋዉንዴሽናችን ይህን ሥራ በስድስት ብሄራዊ ፓርኮች አካባቢ ለመሥራት የጀመረ ሲሆን ልምዱን በፍጥነት ወደሁሉም የሃገራችን ብዝሃ ህይወት ጥበቃ ሥፍራዎች በማስፋት በተለይም ደግሞ ከንጉሱ ዘመን ጀምሮ የተለመደዉና ፓርኮቹን ከአካባቢ ማህበረሰብ ተሳታፊነትና ዘላቂ ተጠቃሚነት ዉጪ ለማስጠበቅ የመፈለግ ዝንባሌ በፓርክ ሀብታችን ላይ እስካሁን ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስ ምክንያት በመሆኑ ይህንን አሰራርና አስተሳሰብ በመቀየር inclusive protected area governance እንዲለመድ የበኩሉን ድርሻ ለማበርከት በማለም ነዉ። ስለሆነም በደቡብና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች በሚገኙ ፓርኮች የታየዉን ችግር መነሻ በማድረግ የተቀመጡ መፍትሄዎችን በጋራ መተግበር በመላዉ ሀገሪቱ በፓርክ ጥበቃና ህብረተሰብ ተጠቃሚነት ላይ ለዉጥ ለማምጣት የሚኖረዉ ፋይዳ ትልቅ በመሆኑ የሚመለከተን ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘን እንደምንሰራና ባጭር ጊዜ ዉጤት ማምጣት እንደምንችል እምነታችን የጸና ነዉ።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችንም በጨበራጨርጨራ ብሄራዊ ፓርክ የተቀናጀ ቡድን በመላክ በፓርኩ ለሚታዩ ችግሮች መፍትሄ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ማድረጋቸዉን በታላቅ አድናቆት የምናይ በመሆኑ ይኸዉ ሥራ በኦሞና ማጎ ብሄራዊ ፓርኮችም እንዲደገም፤ ወደፊትም ደረጃ በደረጃ በጋምቤላና አዋሽ ብሄራዊ ፓርኮችም እንዲቀጥል በአክብሮት እንጠይቃለን።